# DEVELOPMENT
## DBE'S NEWSLETTER

# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ
## ዜና መጽሔት

ቅፅ 2 ቁጥር 4 ሚያዝያ 2007



የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከደንበኞቹ ጋር ምክክር አካሄደ

## በውስጥ ገፆቻችን

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከደንበኞቹ ጋር ምክክር አካሄደ

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሠራተኞች በአዲስ አበባ ከተማ ቀላል ባቡር የሙከራ ጉዞ አደረጉ

ለባንኩ ማኔጅመንት አባላትና ሠራተኞች ስልጠና ተሰጠ

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የእግር ኳስ ቡድን በኢሰማኮ የበጋ ውድድሮች ዋንጫ አነሳ

# ተ ል ዕ ኮ

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ልዩ የፋይናንስ ተቋም ሲሆን ተልዕኮውም የመንግሥት የልማት አቅጣጫን መሠረት በማድረግ አዋጭ ለሆኑ የልማት ፕሮጀክቶች ከሀገር ውስጥና ከውጭ የብድር ገንዘብ በማሰባሰብ የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት ነው፡፡ ይህንን ተልዕኮውንም ሲወጣ የባንኩን ህልውና በማረጋገጥ ጭምር ነው፡፡
ባንኩ ይህ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ተልዕኮው እንዲሳካ፤ ለቀጣይ አቅም ግንባታ፣ ለደንበኛ ተኮር አገልግሎትና ለአካባቢ ጥበቃ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡

# ራ ዕ ይ

በባንኩየፋይናንስ ድጋፍ የሚቋቋሙትን ፕሮጀክቶች በሙሉ እ.ኤ.አ. በ2020 ላይ 100% ውጤታማ ማድረግ፡፡

# እሴቶች

• ለተልዕኮአችን መሣካት ቁርጠኛ ነን
• ለደንበኞቻችን ልዩ ትኩረት አለን
• ሐቀኝነት ዋናው ሃብታችን ነው
• ለቡድን ሥራ ትልቅ ቦታ እንሰጣለን
• ሠራተኞች የባንኩ ተመን የሌላቸው ሐብት ናቸው
• ሁሌም መማር የዕድገታችን መሠረት ነው
• ለአካባቢ ጥበቃ ትኩረት እንሰጣለን

# Mission Statement

*"The Development Bank of Ethiopia is a specialized public financial institution established to provide development finance along with technical support to viable priority area projects by mobilizing fund from domestic and foreign sources while ensuring its sustainability.*
*The Bank earnestly believes that these highly valued objectives can best be served through continuous capacity building, customer focus and concern to the wider environment".*

# Vision

*"100% Success for all Financed Projects by 2020"*

# Values

- *Commitment to mission*
- *Customer focus*
- *Integrity*
- *High value to employees*
- *Learning organization*
- *Team work*
- *Concern to the environment*

## የመንግሥት ፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲና የፋይናንስ ድርጅቶች ሠራተኞች የሕዳሴውን ግድብ ጎበኙ!

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የመንግሥት ፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ እና በሥሩ የሚገኙ የፋይናንስ ድርጅቶች ሠራተኞች ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ በሚካሄድበት ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጉባ በመገኘት ጎበኙ። ግንቦት 27 ቀን 2007 ዓ.ም በተካሄደው የጉብኝት መርሐ ግብር ላይ ከ400 በላይ የሚሆኑ የመንግሥት ፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ፣የኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ተሳትፈዋል።

በጉብኝት መርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው ስለግድቡ አጠቃላይ ሁኔታ ገለጻ ያደረጉት የታላቁ ኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ስመኘው በቀለ የፋይናንስ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በአካል ተገኝተው የግድቡን የግንባታ ሂደት መጎብኘታቸው በግንባታ ሥራው ላይ እየተሳተፉ ለሚገኙ ሠራኞች ልዩ ትርጉም እንዳለው ገልጸዋል።

ኢንጅነሩ አያይዘውም "ከመንግሥትም ሆነ ከግል ተቋማት እየመጡ ጉብኝት የሚያደርጉ ሠራተኞች እዚህ ለምንገኝ ሁሉ ትልቅ ብርታትን ይፈጥርልናል። በጉብኝቱ እየተሠራ ባለው ድንቅ ነገር ተደስተው ሲመለሱ ማየት ለሠራተኞች ከፍተኛ አቅም ይፈጥራል። በዚህ መልኩ ከመንግሥት መስሪያ ቤቶች የመጡ ከ400 በላይ ጎብኝዎችን በአንድ ጊዜ ስናተናግድም ይህ የመጀመሪያው ነው። በተለይም ሕዝቡ ካለው እየቆጠበ ለግድቡ አስተዋጽኦ ያደርግ ዘንድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱት ዋነኞቹ ተዋንያን የፋይናስ ድርጅቶች ሠራተኞች በአካል ተገኝተው ሲጎበኙን ልዩ ደስታ ይሰማናል" ብለዋል።

ስለግድቡ ፋይዳ ሲያብራሩም "... የሕዳሴው ግድብ የፈጣን እድገታችን ዐብይ ማሳያና በዓለም አቀፍ መድረኮች ኢትዮጵያን በክብር እያስጠራት ያለ ተውለብላቢ ሰንደቃችን ነው። በተለይም በራሳችን ሙሉ አቅም እየገነባነው ያለና ግንባታውም የተጋመሰ መሆኑን ተከትሎ ዓለም በአንድ ድምጽ ተባብሮ አገራችንን የፈጣን የኤሌክትሪክ ልማት ተምሳሌትና የአፍሪካ ኩራት መሆኗን እየመሰከረ ነው። ግድቡም ከምንም በላይ አንድነታችንን እያጠናከረልን፣

እርስ በርሳችን እያስተሳሰረንና የይቻላል መንፈሳችንን እያሳደገልን ይገኛል፡፡ ለአካባቢያዊ ጥበቃና ልማትም ጉልህ ሚና ይጫወታል፡፡ አገራችን በአሁኑ ሰዓት በዓለም ተወዳዳሪ የሆነና ከፍተኛ ኃይል የማመንጨት ግስጋሴ ላይ በመሆኗም ሁላችንም ልንኮራ ይገባናል፡፡ የሕዳሴው ግድብ ለአገራችን ሁለንተናዊ ልማት ወርቃማ እድል ነው፡፡” ብለዋል፡፡

በዕለቱ በጉብኝቱ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የመንግሥት ፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ስንታየው ወ/ሚካኤል በአጠቃላይ በግድቡ ግንባታ ላይ እየተሳተፉ ያሉትን ሁሉ አመስግነዋል፡፡ “የመላውን የኢትዮጵያን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አደራ ተሸክማችሁ በዚህ በረሃ ውስጥ በታላቅ ጽናት የሕዳሴያችንን ግድብ እየገነባችሁ ያላችሁ ሁሉ ክብር ይገባችኋል፡፡ እኛም በየአቅማችን በገንዘብ ከማገዝ ባሻገር እዚህ ድረስ በአካል የመጣነው ከጎናችሁ መሆናችንን የበለጠ ልናረጋጥላችሁ ነው፡፡ በተለይም በ24ኛው የግንቦት 20 የድል በዓል ማግስት ግድቡን መጎብኘታችን የመንግሥትና የሕዝብ የጋራ ትግልና የሕዳሴ ጉዞ ብሥራት ማሳያ ነው፡፡ የተጀመረው ፈጣንና ተከታታይ የእድገት ጉዟችንም በጽኑ መሠረት ላይ የተገነባ ነው” በማለት ለግድቡ የሚደረገው ድጋፍ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል፡፡





# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከደንበኞቹ ጋር ምክክር አካሄደ





የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሰኔ 9 ቀን 2007 ዓ.ም. በሒልተን ሆቴል ለግማሽ ቀን ከ85 በላይ ከሆኑ የባንኩ ደንበኞች ጋር ውይይትና ምክክር አካሄደ፡፡

የባንኩ ፕሬዝዳንት አቶ ኢሳያስ ባህረ በመግቢያ ንግግራቸው ለባንኩ ተልዕኮ በተሳካ ሁኔታ መፈጸም የደንበኞች ድርሻ ትልቁን ቦታ እንደሚይዝና በዚህም የባንኩ ዋነኛ ዓላማ ደንበኛ ተኮር አገልግሎት በመስጠት እርካታውን ማሳካት ነው ብለዋል፡፡

አቶ ኢሳያስ አያይዘው "ባለፉት ዓመታት ባንኩ በዚህ መልኩ የጋራ መድረክ በማዘጋጀት መፍትሔ እየሰጠ ወደፊት በመራመድ ላይ ይገኛል" ብለዋል፡፡

የመድረኩ ዓላማም ከዚህ ቀደም በነበረው መድረክ ላይ ለተነሱ ሀሳቦች፣ አስተያየቶችና ጥያቄዎች ምላሽ በመስጠት ውይይት እንዲደረግበት እንዲሁም በሚነሱ ሀሳቦች ላይም በመነጋገር፣ በመደጋገፍና በመተጋገዝ የጋራ መፍትሔ መፈለግ ይሆናል በማለት ተናግረዋል፡፡

በመቀጠልም በምክክር መድረኩ ላይ ከዋናው መስሪያ ቤትና ማዕከላዊ ሪጅን ደንበኞች ጋር ከዚህ ቀደም በተደረገ የምክክርና የውይይት መድረክ መፍትሔ እንዲሰጣቸው ለተነሱ 20 ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ ጽሑፍ በባንኩ የብድር አገልግሎት ምክትል ፕሬዝዳንት አቶ ታደሰ ሐጢያ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡

በጽሑፉ ከቀረቡት ዋና ዋና ሀሳቦች

መካከል በባንኩ ውስጥ የውሳኔ አሰጣጥ ሰንሰለቶች አንጻራዊ በሆነ መልኩ መርዘም፣ በብድር አሰጣጥ ሂደት ውስጥ አንዳንድ ፕሮጀክቶች በልዩ ሁኔታ ቢታዩ፣ የባንኩ አሰራር ውስብስብ እየሆነ መምጣት፣ በዓለም አቀፍ የባንክ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ መሻሻል ቢኖር፣ የደንበኞች ሂሳብ አያያዝ አልፎ አልፎ ግድፈቶች የሚታይበት እና የብድር ሰነዶችም የሚጠፉ በመሆኑ አሰራሩ ቢሻሻል፣ በባንኩ በቂ የመኪና ማቆሚያ ስፍራ አለመኖር፣ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ትኩረት ቢደረግ፣ ለፕሮጀክት ማስፋፊያ የሚለቀቅ ብድር እዳ መመለሻ ጊዜ ቢራዘም እና በባንኩ የፖሊሲ ማሻሻያ ዙሪያ ትኩረት ተሰጥቶ ቢሰራበት የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በዚህም ለተቀላጠፈ የብድር ሥርዓት የብድር አሰራር ሥርዓት ማኑዋል መዘጋጀቱ፣ ትላልቅ ፕሮጀክቶች በሲኒየር ኦፊሰሮች ክትትል እንዲደረግባቸው መደረጉ፣ ለተቀላጠፈ አገልግሎት ለሠራተኞች የክህሎት ሥልጠና መሰጠቱ፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ለደንበኞች የመኪና ማቆሚያ ሥፍራ መዘጋጀቱ፣ የብድር መመለሻ እፎይታ ጊዜ ከአንድ ዓመት ወደ ሁለት ዓመት መራዘሙ ሆኖም ሀሳቡ እንደፕሮጀክቱ ሁኔታ ከመነሻው በፕሮጅክቱ ውስጥ ከተካተተ በልዩ ሁኔታ እንደሚታይ፣ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ባለሀብቶች እየተደረገ ያለው ድጋፍ ተመጣጣኝ መሆኑና በፖሊሲ ማሻሻያ ዙሪያም በባንኩ የፖሊሲ ሰነዶች ተዘጋጅተው የበላይ የመንግስት ኃላፊዎችን ውሳኔ ብቻ እየተጠባበቁ እንደሚገኙ በሰነዱ ተገልጿል፡፡

ከጽሑፍ ገለጻው በኋላ መድረኩ ለውይይትና ምክክር ክፍት የሆነ ሲሆን የተለያዩ አስተያየቶች፣ ሀሳቦችና ጥያቄዎች ከደንበኞች ተነስተዋል፡፡

አብዛኛዎቹ ደንበኞች የባንኩ አሰራር ግልጽነት የሰፈነበት፣ አሳታፊና ዴሞክራሲያዊ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተያያዘም ከተነሱ ጥያቄዎች መካከል 70/30 የብድር አሰራር ለሁሉም ፕሮጅክቶች ስለማይሰራ እንደፕሮጀክቱ ሁኔታ ታይቶ ቢሻሻልና ሀብት/ንብረት (In-Kind) ግምት ውስጥ ቢገባ፣ Working Capital እንደ ሴክተሩ ሁኔታ ታይቶ ቢሰራበት፣ የብድር ገንዘቡ ቶሎ ቢለቀቅልንና የሚለቀቀው የገንዘብ መጠን ከስራው ጋር ተመጣጣኝ ቢሆን፣ የብድር መዘግየት መኖሩ፣ የሀገር ውስጥ

ባለሀብት ቢበረታታ፣ የውጭ ምንዛሪ አሰጣጡ በንግድ ባንክ በኩል መሆኑና አሰራሩም የተጓተተ እንደሆነ፣ ባንኩ ከሌሎችም ባለድርሻ አካላት ጋር ተባብሮ ቢሰራ፣ ግብረ መልስና ስለ ብድር ሁኔታችን /ምን ያህል ብድር እንዳለብን፣ ምን ያህል እንደቀረ፣ የወለድ ምጣኔ፣ወዘተ የሚገልጽ መረጃ /Statement/ ቢዘጋጅልን፣ በገበያ ውስጥ ቶሎ ገብተን እንድንሰራ ባንኩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ቢያግዘን የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከጋምቤላ የእርሻ ኢንቨስተሮች ማህበር በኩል የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ድጋፍ ባያደርግ ኖሮ አብዛኛው ባለሀብት በዛ አካባቢ እንደማይሰማራና ባንኩ ግን ይህን በማድረጉ በአሁኑ ጊዜ የተረጋጋ የልማት ሥራ በክልሉ እንዳለ የተብራራ ሲሆን አሁን ግን የብድር መዘግየት እንዳጋጠማቸውና ባንኩ የብድር ዓይነቶችን ለያይቶ ቢያያቸው የሚል ሀሳብ ተነስቷል።

በምክክር መድረኩ ላይ ለተነሱ ሀሳቦችና ጥያቄዎች አቶ ኢሳያስ ደንበኞች ለባንኩ ይጠቅማሉ የሚሉትን ሀሳቦች በመስጠታቸው አመስግነው ይህን መሰል ስብሰባ በየሩብ ዓመቱ በየክልሉ እንደሚደረግና ከደንበኞችም ጋር የጠበቀ የሥራ ግንኙነት እንዳለ ገልጸዋል።

የፖሊሲ ጥያቄዎችን በተመለከተም የማሻሻያ ሀሳቦችን እያካተትን ለመንግስት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በማቅረብ ላይ እንገኛለን ብለዋል። የ70/30 መዋጮ በተመለከተም ከገንዘብ በተጨማሪ በዓይነትም ቢሆን ብድር እንደሌለበት ከተረጋገጠና ንብረቱ ገቢ የሚያስገኝ ከሆነ ይህን ጥያቄ እናስተናግዳለን፣ ሆኖም 70/30 በፖሊሲ የተቀመጠ ነው ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲሸጋገሩ ባንኩ ትልቅ እገዛ እያደረገ ይገኛል፤ በቀጣዩ ዓመትም በሊዝ ፋይናንሲንግ ፖሊሲ መሠረት ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ለተሸጋገሩ ባለሀብቶች 10 በመቶ አዋጥተው ማሽን እየተገዛላቸው ለማስተናገድ ወደፊትም ኢንዱስትራላይዝድ ሆነው እንዲያድጉ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራበት ይገኛል፤ ይህ ሀገራዊ ፖሊሲም ጭምር ነው በማለት አብራተዋል።

Working Capitalን በተመለከተም ወደ ሁለት ዓመት ከፍ መደረጉንና

የቋሚ Working Capitalን ገና ከመነሻው በፕሮጅክቱ ውስጥ በማካተት እንዲሁም ከባንኩ ባለሙያዎች ጋር በመተማመንና በመግባባት በመስራት መፍትሔ ማግኘት እንደሚቻል ተናግረዋል።

ባለሀብቱ የብድር ሰነዶችን በጊዜ ስለማያሟላ የብድር መጓተት ይታያል፤ ለዚህም ብድሩ በተቀመጠለት 34 ቀናት ውስጥ እንዲፈጸም አስፈላጊውን መረጃ በጊዜ አሟልቶ መቅረብ አስፈላጊ መሆኑን ፕሬዝዳንቱ አስምረውበታል።

በተጨማሪም የብድር ውሳኔዎችን በተመለከተ እስከ 25 ሚሊዮን ብር ድረስ የባንኩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መወሰን እንደሚችሉ፣ የውጭ ምንዛሪን በተመለከተም ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ትኩረት እንደሚደረግ፣ የጋምቤላ አካባቢ እርሻ እየተስፋፋ መምጣቱንና ለዚህም ባንኩ ትልቅ እገዛ እያደረገ መሆኑን፣ ሆኖም በክልሉ የተደራረቡ መሬቶች መኖራቸው እና የተሰጡ ብድሮች ምን ያህል በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋል አለመዋላቸው እየተረጋገጠ ቢሆንም የብድር መዘግየቱ ጉዳት እንዳያደርስ በክትትል እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

በመጨረሻም አቶ ኢሳያስ ይህ ምላሽ የመጨረሻ አለመሆኑንና ችግሮችንም ደረጃ በደረጃ በመፍታት ከባንኩ አቅም በላይ የሆኑትን ደግሞ ለበላይ የሥራ ኃላፊዎች እንደሚያስተላልፉ ተናግረዋል፤ ለባንኩ ለተሰጡት ገንቢ አስተያየቶችም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

## የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሠራተኞች በአዲስ አበባ ከተማ ቀላል ባቡር የሙከራ ጉዞ አደረጉ

ሰባ የሚደርሱ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሠራተኞች ግንቦት 14 ቀን 2007 ዓ.ም. ከሰዓት በኃላ የሙከራ ጉዞ እያካሄደ በሚገኘው የአዲስ አበባ ከተማ



ቀላል ባቡር ትራንስፖርት ከቃሊቲ - ስታዲየም - ቃሊቲ ጉዞ አድርገዋል፡፡

የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት እስከ መጪው መስከረም 2008 ዓ.ም. ድረስ የሙከራ ጉዞ በማድረግ በመጪው ዓመት ሙሉ ለሙሉ አገልግሎት መስጠት እንደሚጀምር የሚጠበቅ ሲሆን በሙከራ ጉዘው ከአገልግሎቱ ጋር የተያያዙ ግብረ መልሶችን በጹሑፍ መጠይቅ ይሰበስባል፡፡

በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሠራተኞች ከጉዟቸሁ በኃላ የቀረበላቸውን የጹሑፍ መጠይቅ በመሙላት ስለ አገልግሎቱ እንዲሁም ስለ ታሪፍ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

ጉዞው የተዘጋጀው በኢትዮጵያ ልማት ባንክና በኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን የጋራ ትብብር ሲሆን ጉዞው ስለ ባቡር አጠቃቀም ግንዛቤ ያስጨበጠ እንደነበር ተሳታፊ የነበሩ ሰራተኞች ተናግረዋል፡፡






## ለባንኩ ማኔጅመንት አባላትና ሠራተኞች ስልጠና ተሰጠ

150 ለሚሆኑ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሥራ ሂደትና ቢሮ ሥራ አስኪያጆች፣ ለፕሪንሲፓል ኦፊሰሮች፣ ለቅርንጫፍና ንዑስ ቅርንጫፍ መ/ቤት ኃላፊዎች በአራት ዙር (ከሚያዚያ 09 እስከ ግንቦት 29 ቀን 2007 ዓ.ም.) "Employee Engagement and Managing Young Employees" በሚል ርዕስ 5ኛ ፎቅ ላይ በሚገኘው የባንኩ አዳራሽ ስልጠና ተሰጥቷል።

የመጀመሪያው ዙር ሥልጠና ከአቪዬሽን አካዳሚ በመጡ ባለሙያዎች የተሰጠ ሲሆን ከሁለተኛው እስከ አራተኛው ዙር ያሉት ሥልጠናዎች ደግሞ የመጀመሪያውን ሥልጠና በተከታተሉ የሰው ሐብትና ልማት የሥራ ሂደት ባለሙያዎች አማካይነት ተሰጥቷል።

የስልጠናው ዓላማ በባንኩ ውስጥ ያለውን የሰራተኞች የስራ ላይ ተሳትፎ ወይም "ኢንጌጅመንት" (Engagement) ያለበትን ሁኔታ በማወቅ የተሻለ የ"ኢንጌጅመንት" ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል አቅምና ዝግጁነትን በሥራ መሪዎች ላይ ለመፍጠር እንዲሁም ባንኩ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየቀጠረ የሚገኘው ወጣት ሠራተኞችን እንደመሆኑ መጠን ከዚህ አንጻር ያለውን የትውልድ ክፍተት (Generation Gap) ግምት ውስጥ ያስገባ የአመራር ጥበብ ለሥራ ኃላፊዎች ለማስጨበጥ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

በስልጠናው የተካተቱ ዋና ዋና ርዕሶችም፡- The Concept and Importance of employee engagement, Measuring level of engagement, Characteristics of engaged employees, Factors leading to employee disengagement, Drivers of employee engagement, Improving and Sustaining employee engagement in DBE, Actors in employee engagement, Engaging different generations at work, እና DBE and the generations at work, የሚሉት ናቸው።

ከስልጠናው በኋላ ሰልጣኞች ስልጠናው በባንክ ደረጃ ያለውን የ"employee engagement" እና "generation gap" ለማየት ያስቻለና ሰራተኞች ሥራቸውንና የስራ ቦታቸውን ወደው በእኔነት ስሜት የሚሰሩበትን ሁኔታ በማመቻቸት ረገድ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት እንደሚያግዛቸው ተናግረዋል።

በተጨማሪም የሥልጠናው ሂደት የተሳካ መሆኑንና በተለይ ከሁለተኛው ዙር በኋላ የነበረው ሥልጠና በውስጥ አቅም መሰጠቱ ለወደፊቱ ተጨማሪ ሥራ መስራት የሚያስችል የውስጥ አቅም መኖሩን የሚያሳይ ነው የሚል አስተያየት ተሰጥቷል።

# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የእግር ኳስ ቡድን በኢሰማኮ የበጋ ውድድሮች ዋንጫ አነሳ

የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሠማኮ) ባዘጋጀው የ2007 ዓ.ም የበጋ ውድድሮች የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የእግር ኳስ ቡድን ሰኔ 7 ቀን 2007 ዓ.ም ከፓላሬስና ልጆቹ ጋር ባደረገው የፍፃሜ ጨዋታ 4-0 በማሸነፍ የዋንጫ አሸናፊ ሆኗል። ቡድኑ ለዋንጫ የደረሰው ከኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ጋር ባደረገው ጨዋታ 3-1 በማሸነፍ ነው።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዝዳንት አቶ ኢሳያስ ባህረ በውድድር ቦታው በመገኘት ከተጨዋቾች ጋር የተዋወቁ ሲሆን ቡድኑን አበረታተዋል፤የዕለቱንም ጨዋታ አስጀምረዋል።የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሠራተኞችና የማኔጅመንት አባላትም በሙገር ሲሚንቶ የእግር ኳስ ሜዳ በመገኘት ለቡድኑ ያላቸውን ድጋፍ አሳይተዋል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የእግር ኳስ ቡድን አሰልጣኝ አቶ አልታዬ አበበ በውጤቱ መደሰታቸውንና ወደፊትም ቡድኑን የበለጠ በማጠናከር በተመሳሳይ ውድድሮች የባንኩን ስም ለማስጠራት መዘጋጀታቸውን



ገልፀዋል፡፡

የባንኩ የእግር ኳስ ቡድን 25 አባላት ያሉት ሲሆን አባላቱ በባንኩ በተለያዩ የስራ ክፍሎች የሚሰሩ ሠራተኞች ናቸው፡፡ የኢሠማኮ ውድድሮች ህግ በሚፈቅደው መሠረት ሁለት ተጫዋቾች ከተቋሙ ውጪ ቢሆኑም ባላቸው ችሎታ ተመርጠው በቡድኑ እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡የእግር ኳስ ቡድኑ ቋሚ የልምምድ ጊዜ ያለው ሲሆን ማክሰኞ፣ሐሙስና ቅዳሜ ልምምድ ያካሂዳል፡፡ባንኩም ለጨዋታ አስፈላጊ የሆኑ ትጥቆችንና ሌሎችን ድጋፎችን የ185 ሺህ ብር በመፍቀድ ያሟላ ሲሆን ድጋፉ ለውጤቱ እንዳገዛቸው ተጨዋቾቹና አሰልጣኙ ገልጸዋል፡፡የባንኩ የሰራተኛ ማህበርም ለተጨዋቾች የላብ መተኪያ በሚል በጀት መድቦ ሲንቀሳቀስ የቆየ ሲሆን ከአዘጋጁ አሠማኮ ጋር ግንኙነት በመፍጠርና ውድድሩን በበላይነት በመምራት እየተሳተፈ ይገኛል፡፡

በሁለተኛ ዲቢዝዮን በተደረገው በዚህ ውድድር 13 በኢሠማኮ የታቀፉ የግልና የመንግስት ተቋማት ተሳታፊ ሆነዋል፡፡በመጪው የውድድር ዘመን የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ባገኘው ውጤት መሰረት በአንደኛ ዲቢዝዮን ውድድሩን ያካሄዳል፡፡

# የምስል ዜናዎች

የመንግሥት ፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲና የፋይናንስ ድርጅቶች ሠራተኞች የሕዳሴውን ግድብ ጎበኙ!





# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከደንበኞቹ ጋር ምክክር አካሄደ





# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሠራተኞች በአዲስ አበባ ከተማ ቀላል ባቡር የሙከራ ጉዞ አደረጉ





የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

DEVELOPMENT BANK OF ETHIOPIA

Tel:251-11-551-1188/89 Fax: 251-11-551 1606
Email: dbe@ethionet .et / Website : www.dbe.com.et